## *የሙታን አጽም ጥሪ*




ላለፉት 35 አመታት በመለስ ዜናዊና አጋሮቹ የተፈጁት ሙታን ድምጽ ይጣራል:

- ወያኔ ጫካ በነበረ ጊዜ የመለስንና አጃቢዎቹን አላማ አንደግፍም በማለታቸው ብቻ በመለስ ዜናዊና አጃቢዎቹ የተፈጁት የትግራይ ልጆች አጽም ይጮኸል
- በበደኖ፣ በወተር የተፈጁት ገደል ከነህይወታቸው የተወረወሩት በአርባ ጉጉ በተዘጋ ቤት የተቃጠሉት ህጻናት፣ አረጋውያን፣ ሴት፣ ወንድ የአማርኛ ተናጋሪዎች አጽም ይጮኸል
- ገና ለገና ስልጣኔን ሊቀናቀኑኝ ይችላሉ በማለት በየቦታውና በየስርቤቱ የተፈጁ የኦሮሞዎች አጽም ይጮኸል
- የሞት ቀን ዛሬ ነው በማለት የሞት አዋጅ ተውጆባቸው የረገፉ የአኝዋኮች አጽም ይጮኸል
- የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው በመንገዝ ላይ እያሉ የተፈጁት የሲዳማዎች አጽም ይጮኸል
- መብቴ ይከበር ማለት እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው በጠራራ ጸሐይ የተፈጁ የአዲስ አበባ ህዝቦች አጽም ይጮኸል
- የጎሳ ግጭት ነው በማለት ሽፋን የተፈጁት የከፌቾ ሸከቾ አጽም ይጮኸል
- በታቸው ተቃጥሎ፣ በዶዘር ተጠርጎ አሸዋ የለበሱ የህጻናት፣ የአረጋውያን፣ የወንድ የሴት ኦጋዴኖች አጽም ይጮኸል
- በውክልና ጦርነት ተዘምቶባቸው ያለቁ የሱማሌዎች አጽም ይጮኸል

***አጽሞቹ ደግሞ ዘር የላቸውም፣ ሐይማኖት የላቸውም፣ ክልል የላቸውም፣ ከማንም ጽብ ዝምድና የላቸውም ሁሉም ግን በአንድ ድምጽ ይጮኸሉ መልዕክታቸውም:***

- ደማችን በከንቱ ፈሶ እንዳይቀር፣ ወንጀለኞቹ ለፍርድ እንዲቀርቡ በአንድነት እንድትጮሁልን በረገፈው አጽማችን እንጠይቃችኋለን:
- ለዚህም September 13 2009 በሚደረገው ስልፍ ላይ ሁላችሁም ተገኙልን:

- እኛ አጽማችን የረገፈው ወንጀል ስርተን አይደለም በሐገር ቤት ያሉ ወገኖቻችንም ደግሞ ለረገፈው አጽማችን ሊጮሁልን አይችሉም: ቢጮሁ የኛ እድል ይጋጥማቸዋል እናንተ ግን ከዚህ ሁሉ ነጻ ናችሁና ድምጽ ሁኑን:
- አጽማችን አጽም ነው ዘር፣ ክልል፣ ሐይማኖት፣ ጾታ ለአጽማችን ትርጉም የለውም የወል ስማችን ግን የሰው አጽም ነው በመሆኑም እናንተም ክልል፣ ቋንቋ፣ ዘር፣ ጾታ ሳትሉ በሰውነታችሁ ብቻ በአንድነት ጩሁልን:
- የኛ የረገፈ አጽም ይበቃ ሌላ አጽም እንዳይረግፍ የቻላችሁትን ሁሉ አድርጉ ነው:

## ታዲያ

*የአጽሞቹን ጥሪ ለማዳመጥ ዝግጁ ነን?*

*ራሳችንን ከህሊና ወቀሳ ለማዳን ዝግጁ ነን?*

*የወንጀለኞችን የፍርድ ቀን ለማፋጠን ዝግጁ ነን?*

*ተጨማሪ የሌላ ወገኖቻችን አጽም እንዳይረግፍ እንፈልጋለን?*

**ከሆነ** September 13 2009 D. C **እንገናኝ**

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቅ